# ትንሽ ስለ ተስፋዬ ገ/አብ (ዳግማዊ መርቆሬዎስ)

ከሚካኤል ሰይፉ

"የጋዜጠኛው ማስታወሻ" የሚለው መጽሐፍ በኢንተርኔት ተሰራጭቶ መነጋገሪያ አርዕስት ከሆነ ሰንበትበት ብሏል። ተስፋዬ ገ/አብ ቀደም ብሎ ከፃፈው መጽሐፍ ተብዬው አንዱ "የቡርቃ ዝምታ" ሲሆን፤ የጥላቻና የርስ በርስ ግጭትን እንዲጭር ተደርጐ ለልዩ ዕኩይ ተልዕኮ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ነበር። ሆኖም ከጥንት ጀምሮ ተሳስቦና ተከባብሮ የሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በበሰለ አመለካከቱና በሰከነ አስተዋይነቱ ይሄንን መጽሐፍ ከመጤፍ ሳይቆጥረው አጣጥሎት የጸሐፊውን ምኞት አክሽፎታል።

እራሱ ጸሐፊው በገጽ 221 ላይ እንደገለጸው ከበረከት ስምኦን ጋር ባለመስማማቱ ከአገር እንዲወጣ ገፋፍተውት፤ በአስርት ሺህዎች በሚቆጠር ወጪ የመሸኛ ድግስ በዋቢ ሸበሌ ሆቴል ተደርጎለት በቦሌ የአየር ማረፍያ በኩል ከኢትዮጵያ በሰላም ወጥቷል። እነሆ ይህ ግለሰብ አድብቶ ከመሸገበት ጎሬው ከዓመታት በኋላ በ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" መጽሐፍ ቢጤው ሊያናግረን ብቅ ብሏል።

ወደፊት ስለዚህ መጽሐፍ በግምገማ መልክ እመለሰበታለሁ። ለጊዜው ይቺን መግቢያ እንድጭር ወደ ገፋፋኝ ነጥብ ልመለስ። በዚሁ መጽሐፍ ገፅ 61 ላይ ደራሲው ከዚህ በፊት ይጠቀምበት የነበረውን የብዕር ስም ሲገልጽ፣ "...ደራሲ ብርሃኑ ዘርይሁንን ለማስታወስ የሱን የብዕር ስም በመውሰድ "ዳግማዊ መርቆሬዎስ" በሚል ስም ደርግን የሚያጋልጡ ቀስቃሽ ፅሁፎችን ማንጎድጎድ ጀመርኩ።..." ይላል። እኔም ይህ መሠሪ ግለሰብ በሌላ ሰው ስም ሸፍን ለፃፈው ፅሑፍ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚታተም የነፃው ፕሬስ መጽሄት ላይ ምላሽ ተሰጥቶት ማንበቤ ትዝ አለኝና፤ የሰውዬውን ባህርይና ድርጊት በተለይ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በበለጠ እንዲረዱት አንድ ነባራዊ መረጃ ላቀርብ ወሰንኩ።

በሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ በነሐሴ 30 ቀን 1985 ዓ/ም ባወጣው ዕትሙ ይዞ ብቅ ያለው ጽሑፍ ርዕሱ "ውሾቹ ይጮኻሉ ግመሉ ጉዞውን ቀጥሏል" ይላል። ይህን አባባል እስከዛሬ ድረስ ወያኔዎች፣ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ለመስደብ የሚጠቀሙበት ፀያፍ አባባል ሲሆን የፃፈውም ይኸው ተስፋዬ ገ/አብ (ዳግማዊ መርቆሬዎስ) ነበር። በነገራችን ላይ ይሄንኑ አባባል እነ ወ/ሮ ብርቱካን ሚደቅሳ ቅንጅትን ለማፍረስ በዳያስፖራው ከአገር አገር እየተዘዋወሩ በየመድረኩ በሚለፍፉበት ጊዜ በካናዳ፣ ካልጋሪ በእነ ብዙ ወንድም አገኘ (በፓልቶክ ስሟ ሙያዬ ምስክር) አጨብጫቢነትና ይደገም ባይነት በአደባባይ ሕዝብ በተሰበሰበበት መድረክ ላይ ደጋግማ ብላዋለች። ብርቱካን ታማኝ ወያኔነቷን ስታረጋግጥልን ነበርና ያው እሷ የመሰረተችው የተቃዋሚ ፓርቲ አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ተብዬው ጓዙን ጠቅልሎ ወደ ወያኔ ካምፕ ገብቷል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የአስራ አራቱ ዓመት የግመሉ ጉዞ ወደ ጥፋት በመሆኑ ተማሮ ነበርና በአገኘው ትንሽ አጋጣሚ በግንቦት 97 ምርጫ ጎሰኝነትን እንቢ ብሎ የግመሉን አከርካሪ አጥንት አሽመድምዶ ኢትዮጵያዊ አንድነትን መረጠ። ታዲያ ዛሬ በመረጥከው አትመራም ተብሎ ትንቅንቅ ላይ ይገኛል። ዛሬም ነገም ድምፄ ይከበር! የምርጫ ቅድመ ሁኔታዎች ሳይመቻቹ ሌላ ምርጫ አይታሰብም እያለ ነው። በዲያስፖራ የሚገኘውም ኢትዮጵያዊ እንደ ደጋፊነት የሕዝብን ድምፅ ማስተጋባት ነው ያለበት።


የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስና አባላቱ በዚያን ጊዜ ወያኔ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ያካሄደውን የጥፋት ዘመቻ በቆራጥነት ተፋልመዋል። በወቅቱ የወያኔ ካድሬና ሹም ሆኖ የጎሰኝነት መርዙን ሲረጭ ለነበረው ለወያኔው/ለሻቢያው ተስፋዩ ገ/አብ (ዳግማዊ መርቆሬዎስ) በሚል ስያሜ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ላሳተመው ጽሑፍ በአንድ መጽሔት ላይ ከሕዝብ ወገን የቆመ ዕውነተኛ ኢትዮጵያዊ የሰጠው ምላሽ ከዚህ በታች እንዳለ ቀርቧል።

የምትጠራጠሩ ካላችሁ ሀቁ ይሄ ነው፤ ተስፋዬ ገ/አብ በጎጠኝነት ቫይረስ የተለከፈ የወያኔ ካድሬ፣ የሻቢያ አገልጋይና የጥላቻ አራማጅ ፀሀፊ ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!! ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች!!

# ጦቢያ

2ኛ ዓመት ቁጥር 6 መስከረም 1986



## ሲባው

# ሙዳ ሙዳ ሥጋ እየጣለ ሥርቆቱን ቀጥሏል

ከሰውነት መልካሙ

አንዳንድ ጓደኞቼ «ሬዲዮና ቴሌቪዥን እንዴት ታዳምጣለህ? ጋዜጦችስ እንዴት ታነባለህ?» የሚሉ ፈሊጥ አላቸው:: የመንግሥት መገናኛ ብዙሃንን ማለታቸው መሆኑ ይገባኛል:: ምክንያታቸውም ግልጽ ነው:: «ይህ ሕዝብ ከሚከፍለው ታክስ በሚመደብ በጀት የሚካሄድ የመገናኛ አውታር የሕዝብ ድምፅ መሆን ሲገባው ልክ እንደዘመነ ደርግ በአንድ የፖለቲካ ድርጅት እጅ ወድቆ ይህ ድርጅት የሚያምንበትን የፖለቲካ መስመር ብቻ ማራመጃና ግለሰቦችንና ድርጅቶችን መዝለፊያ ሆኗልና ማንበቡ፣ ማዳመጡ ምን ፋይዳ አለው?» ለማለት ነው::

አባባላቸው ትክክል አይደለም አልልም:: «አላነብም፣ አላዳምጥም» ማለታቸውን ግን አልቀበለውም:: «ለመደገፍም ለመቃወምም፣ ማወቅ» የሚል እምነት አለኝ:: እና ጋዜጣና መጽሔቶቹን አገላብጣለሁ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አዳምጣለሁ፣ ባለኝ ጊዜ:: አልፎ አልፎ የሚገርሙኝም የሚያሳዝኑኝም ሀሳቦች ያጋጥሙኛል::

አንድ እሁድ ቀን ዕለተ ሰንበት. አዲስ ዘመን፣ ነሐሴ 30 ቀን 1985 ዓ.ም የታተመ ጋዜጣ ሳገላብጥ ዓይኔ አንድ ጽሑፍ ርዕስ ላይ አረፈ:: «ውሾቹ ይጮኻሉ ግመሉ ጉዞውን ቀጥሏል» ይላል:: ፀሐፊው ዳግማዊ መንቆርቆስ ይባላሉ:: አነበብኩት:: በጽሑፉ ውስጥ ተቃዋሚ ወገኖች - ጎሹ ወልዴ፣ መንግሥቱ ኃ/ማርያም የዋሽንግተን ወይም የሉስአንጀለስ የፖለቲካ ቁማር ቁማሪዎች፣ የፈረንጅ አገር ታክሲ ነጂዎች፣ «የሰላምና የእርቅ ጉባዔ» ጠሪዎች፣ የነፃው ፕሬስ ጸሐፊዎች፣ የደርግ ኢሠፓ ፕሮፓጋንዲስቶች ተጠቅሰዋል:: የሚጮኹት « ውሾች» መሆናቸው ነው:: ያልተሰጣቸው መጥፎ ቅጽል የለም:: በአንጻሩ «የኢሠፓን አከርካሪ አጥንት አድቅቆ፣ ሰላምና ነፃነትን ለሕዝቡ አስጨብጦ ሰላምን ያሰፈነው፣ በየክልሉ ልማቱን ያጥለቀለቀው የኢሕአዴግ «ድል» ተዘርዝሮአል:: የኢሕአዴግ ለውጥ ጉዞውንም ቀጥሏል:: ግመሉ መሆኑ ነው:: ይገርማል! «ከኢትዮጵያ የበቀልኩ ነኝ» ከሚል፣ ስለኢትዮጵያ ልማትና ዕድገት ከሚናገር፣ ቢያንስ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት፣ ይሉኝታና ሥነምግባር የተላበሰ ሀሳብ እጠብቅ ነበር:: የፖለቲካ ተቃዋሚ መሆን «ውሻ» የሚል ተራ ስድብ የሚያሰጥ ከሆነ ያለነው በዲሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ ሳይሆን በእረኞች እንካ ሰላንትያ ውስጥ ነው ማለት ነው፣ ምክንያቱም በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መቻቻልና መከባበር አለ:: ታዲያ በዚያ ዓይነት እነያ ጓደኞቼ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃንን ቢጠሉ ምን ይፈረድባቸዋል? ስለስድቡ ይህን ካልኩ ዘንድ በጽሁፉ ስለሰፈሩት ሀሳቦች አንዳንድ አስተያየቶች አሉኝ::

ዳግማዊ መንቆርቆስ ለጽሑፋቸው የሰጡትን ርዕስ ሳሰላስል እኔም የሌቦች የሥርቆት ሥልት ትዝ አለኝ:: ሌቦች በሌሊት ቤት ለመሰርሰር ወደ ሰው ግቢ ሲገቡ ሙዳ ሙዳ ሥጋ ለውሾች እየወረወሩ ነው:: እናም ዛሬ ታሪካዊ ጠላቶቻችን፣ የረጅም ታሪካችን፣ የአንድነታችን፣የአገራችን ሀብት ሌቦች ሙዳ ሙዳ ሥጋ ለአበላ ባዮች እየወረወሩ ሥርቆታቸውን እየቀጠሉ መሆናቸው ታሰበኝ:: ዳግማዊ መንቆርቆስም አንድም ከሠራቂዎቹ ወይም ሙዳ ሥጋ ከሚጣልላቸው አበላ ባዮች ናቸው የሚል ግምት አደረብኝ:: ስለዚህ ነው ለዚያ ሥነ ምግባር ለጐደለው ጽሑፋቸው ትንሽ ሥነምግባር የጐደለው ምላሽ ያስፈልገዋል ብዬ የወሰንኩት:: «ሌባው ሙዳ ሙዳ ሥጋ እየጣለ ሥርቆቱን ቀጥሏል» አልኩት የጽሑፌን ርዕስ:: ለማንኛውም አንባቢን ከፍተኛ ይቅርታ እጠይቃለሁ::

ዳግማዊ መንቆርቆስ « ይህ ትውልድ ምን ሠራ?» ብለው በውጭ አገር ቢሐፉ ያስጠይቁናል::እኔ የኢትዮጵያን የአሁን ትውልድ በደምሳሳው(በጥቅሉ) አልኮንንም:: በጎም መጥፎም ጎኖች አሉትና:: በዚህ ጽሑፍ «ይህ ትውልድ» ስል የዳግማዊ መንቆርቆስን ትውልድ ማለቴ ይታወቅልኝ:: ከቅርብና ከሩቅ የአገሪቱ ጠላቶች ሙዳ ሙዳ ሥጋ እየተወረወረለት የእናት አገሩን ጓዳ ጉድጓዱና ገበና ወለል አድርጐ ለጠላት የከፈተውን የወገን ጠላት ትውልድ ማለቴ ነው:: «ወደድንም ጠላንም የሚያኮራ አገር የለንም:: ኢትዮጵያ ብለን በድፍረት ለመናገር የሚያስችል አገራዊ ሁኔታም ከቶ የለም::» መንቆርቆስ እንደሚሉን ልክ ነው:: ዕድሜ ለእርሳቸው ትውልድ:: የድፍን ኢትዮጵያ ልጆች አፅም ለዓመታት የተከሰከሰባት ኤርትራ ዛሬ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም:: የእምባገነኖችና የጠመንጃ አምላኪዎች ፍላጐት የሕዝብ ፍላጐት ነው ተብለን አብሮ የኖረ ሕዝብ ተለያይቷል:: ከአብደራፊ እስከ መተማ፣ ከሁመራ እስከ ቋራ ያለው የኢትዮጵያ አካል የውጭ ኃይል እየፈነጨበት ዜጋው እየተሳደደ መሆኑ እየተነገረ ነው::ነገ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ምን እንደሚሆን ማናችንም አናውቅም:: ብቻ መንቆርቆስ እንዳሉት ስለ ምናውቃት አገር የምንናገርበት ሁኔታ ዛሬ የለም:: የመንቆርቆስ ትውልድ ምስጋና ይግባውና!

ይህ ትውልድ ታዲያ ምን ያልሠራው ነገር አለ? የኢትዮጵያን ወጣት ምሁር በሰላማንትና ዲሞክራሲ እያናገረ የራሱን ዓላማ አላራመደም?ነገር ታሪክ ያላትን እናት አገሩን በመብትና ነጻነት ስም አልናደም? ያለፈ ታሪካችንን አላንቋሸሸም? ለእኔ ይህ የዳግማዊ መንቆርቆስ ትውልድ የአባትና የአያቶቹ የሆነውን ሁሉ የሚንቅ፣ ራሱ ግን እንዲት ቅንጣት በጎ ነገር ለዚች አገር ያልሠራ፣ ይልቁንም የተሠራውን የሚንድ ትውልድ ነው:: ለነገሩማ ብርቅና ድንቅ ያለፈ ታሪካችን፣ ያለፉ ጀግኖቻችን በመጣጥፍና ንግግሮች የሚጠቀሰው እንዲያው በዲስኩሮች ሁሉ «ለመወሸቅ» አይመስለኝም:: ምሳሌነታቸው የዳግማዊ መንቆርቆስን ትውልድ አዙሮ የሚያይ አንገት ይሰጠው እንደሆን በማለት ነው::ሊላም ማለት ይቻላል:: የታሪካችንና የጀግኖቻችን መዘከር፣ዛሬ በአገሪቱ ላይ እየደረሰ ያለው ተዳምሮ «የታላቁን የአርበኝነት ትግል» ስሜት በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሕሊና እየጫረ ነው፣ ጠረኛ ባትሉኝ::እና አንድ ቀን ኢትዮጵያ እንደገና የምንኮራባት አገር ትሆናለች የሚል የፀና እምነት አለኝ::

ዳግማዊ መንቆርቆስ እንደሚመኙት በአገራችን መንደሮች ሁሉ ውሃ፣ ክሊኒክ፣ መብራት፣ መገናኛ ፋብሪካ ቢያጥለቀልቅ ማን ይጠላ ነበር? ግና በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል?በጥባጩ ማነው? ተግባር ከቃል የበለጠ ይናገራል:: «አያት ቅድመ አያቶቼ ያጡት ዙፋንና ሥርዎ መንግሥት ተመልሰልኛልና ይህን ድሌን የሚቀናቁን ሁሉ ወዮለት!» እያለ ጧት ማታ በክላሽና በቦምብ የሚያስፈራራው የዳግማዊ መንቆርቆስ ትውልድ ካልሆነ እንግዲህ በጥባጮች እኒያ ግመሉን ከጉዞው ለመግታት «የሚጮሁት ውሾች» ናቸው ብዬ ማመን ሊያርብኝ ነው::

በጥባጩ ማንም ይሁን ማን ዛሬ የአንድ አገር ልጆች ጣት እየተቆሳሰርን በምንወነጃጀልበት ሁኔታ ሰላማዊ የአገር ግንባታ እንዴት ሊኖር እንደሚችል ለእኔ ገና አልተገለጠልኝም። ስለ ቀድሞ ታሪክ ሲወሳ፣ ስለ ኢትዮጵያዊነት ሲዘከር እየተንገሸገሸ፣ በጉሣ ፖለቲካ ሰክሮ ሕዝብን ከሕዝብ በሃይማኖትና በጉሣ ለመለያየት፣ የራሱን የሥልጣን መንበር ዕድሜ ለማራዘም ሌት ተቀን የሚቃትት፣ ኃላፊነት የጐደለው የዳግማዊ መንቆርዮስ ትውልድ ባለባት ድሃዋ ኢትዮጵያ በልማት ወደፊት የምትራመድበት ሁኔታ ይኖራል ብዬ አልገምትም።

ዳግማዊ መንቆርዮስ እምነው ሊያሳምኑን የሚፈልጉት ጦርነት ከደርግ ጋር አብሮ የተቀበረ መሆኑን ነው። የሰላምና የግንባታ ዘመንም መጥቶልናል። ይህ ከሆነ እሰዬው።ሁላችንንም ያስደስተናል! ሰላምን ማን ይጠላል? ሐቁ ግን የተባለው ይሆን? አይመስለኝም። ሰላምን በመሻት ብቻ ሰላም አይገኝም፣ ከምኞትም አያልፍም።ከጦርነት ለመውጣት መጀመሪያ የጦርነትን ምንጭ ማድረቅ የግድ ነው። የጦርነት ምንጭ ያለው ደግሞ በፖለቲካው ሠፈር ነው።ጦርነት የፖለቲካ ዓላማ ማስፈፀሚያ ሌላው መንገድ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ዳግማዊ መንቆርዮስ እንዳደረጉት ስለ አገሬ እኔም የምለው አለኝ የሚሰጡን ሁሉ ስም እየሰጡ፣ግራና ቀኝ እየጉንተሉና በጡንቻ እያስፈራሩ ሰላምን መሻት ወይም ሰላም አለ ብሉ ለማመን መሞከር ሞኝነት ነው። ለዳግማዊ መንቆርዮስ ትውልድ ፍላጐት ያልተገዛውን ሁሉ «በሚገባው ቋንቋ» የማናገሩን መንገድ መከተል ለጊዜውም ቢሆን ሳያዋጣ አይቀርም፣ ለተባባሪዎችና እበላ ባዮች ሙዳ ሙዳ ሥጋ እየወረወሩ።

ዳግማዊ መንቆርዮስ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ጉዞ አበረታች መሆኑን የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን የተለመደውን አባታዊ ቡራኬ ሰጥተዋልና ተቃዋሚዎችም፣ ነፃው ፕሬስም እርፋችሁ ተቀመጡ ሊሉን ይሞክራሉ። ግን እስ ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነውና ሕመማችንን የምናውቀው እኛው የአገሩ ሰዎች ነን። በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚያውቀው ራሱ ሕዝቡ ነው።

ከተሞቻችን፣ የመኖሪያና የመሥሪያ አካባቢዎቻችን ክላሽና ቦምብ ባገመደሉ የጦር ሜዳ ሰዎች ተከበው፣ ጦር ሜዳ ያለን እየመሰለን ሌት ተቀን የምንባንንበት ሁኔታ ባለበት፣ ሰዎች ያለ ሕግ እየታሠሩና እየተገደሉ፣ በነፃው ፕሬስ ላይ የአፈና አደጋ አንዣቦ እያለ፣ድምጻችንን ባልሰጠንበት መንግሥት እየተገዛን አንፈልግህም በማንልበት፣ስለአገራችን የወደፊት ዕድል በማንወስንበት ሁኔታ እያለን ስለዲሞክራሲያዊ ሂደቱ አበረታችነት ቢመሰክርልን ሐሰት መስካሪዎችን ከምንታዘብ በቀር የማንንም አመለካከት አይለውጥም።ምናልባትም ለፕሮፓጋንዳ ይጠቅማል ተብሉ ከሆነ ይጻፍበት፣ ዜናም ይሠራበት እኛም እናነባለን፣ እናዳምጣለን። ሁኔታችንን የምናውቀው ግን እኛው ነን።

ወገኑን ምን ያናግረዋል ቢሉ በውስጡ ያለው ድንጊያ። እኛም የሚያናግረን በውስጣችን ያለው ችግር ነው። ችግራችንን ደግሞ ከክሊንተን ይልቅ እኛ በሚገባ እናውቀዋለን። አለበለዚያማ እርፈን የመጣልንን ዲሞክራሲ ባጣጣምን።

አንድ ነገር ለመናገር ይቻላል። ለአንድ አገር ጉዳይ የውጭ ሁኔታና ኃይል ምናልባት መጠነኛ አስተዋጽኦ ከሚኖረው በቀር ወሳኝ ሆኖ አያውቅም። ይህ በሆነ ዛሬ የጐረቤታችን ሱማሌ ችግር በተፈታ። ወሳኝ ራሱ የአገሬው ሕዝብ ነው።«ቢል ክሊንተን መስክረውልናልና እርፋችሁ ተቀመጡ» ያሉት የማይጥመኝ ለዚህ ነው።«ሰላም አለኝ፣ ዲሞክራሲያዊው ሂደት ተስማምቶኛል» ማለት ያለበት ራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።ይልቅስ እርስ በርስ መካሰሱን ትተን ስለ አገራችን ጉዳይ በጋራ እንምከር፣ በአገራችን ብሔራዊ እርቅ ይውረድ። ሙዳ ሥጋ እያቀበሉና እየተቀበሉ በአገርና በሕዝብ ጥቅም ላይ መሠራቱ ያቁም።በአገራችንና በእኛም በዜጎቿ ላይ እያንዣበበ ያለውን አደጋ ማስወገድ የምንችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ■